# ራስታዎችና እምነታቸው

## መግቢያና ማንነት

የራስታዎች ንቅናቄ ወይም ሃይማኖት ከተጀመረበት ከጃሜይካ ቀጥሎ እንደ ሰዎቹ የተስፋ አገር በምትታየው በኢትዮጵያ በቂ ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባው ነበር። በአገራችን ግን ይህ ሃይማኖት ወይም እንቅስቃሴ በአብዛኛው ከስም ያለፈ የታወቀ አይደለም። እኔም ልናዘዝ፤ እነዚህን ሰዎች በስም ከብዙ ዓመታት በፊት ባውቅም እስከ ቅርብ ጊዜ ከስም ያለፈ ጥቂት እንጂ አላውቃቸውም ነበር። በቅርቡ ራስታ የሆነ አንድ ጃሜይካዊ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ለወርልድ ቪዥን ልጆችን እስፖንሰር ለማስደረግ በር እያንኳኳ መጣና የመጣበትንም ጉዳይ እያካሄድን ስለ እምነትና ስለ ክርስቶስ ማውራት ጀመርን። በአማርኛ ያነበብኳትን ስለ ራስታዎች ማንነትና ስለ አምልኮአቸው የተዘጋጀች አንዲት ታናሽ መጽሐፍ አስታወስኩ። ከዚያ የማስታውሰውን አንዳንድ ጉዳዮችም መንደርደሪያ በማድረግም አወራን። ከዚህ ሰው ጋር ካወራንና በኢትዮጵያም ስላለው ሁኔታ በመጠኑ ከተረዳሁ በኋላ ነው ይህችን መጣጥፍ የጻፍኩት። እስከማውቀው በአማርኛ አንዲት መጽሐፍ ብቻ ነው ያየሁት። እርስዋም የወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ የሱስ የወጣቶች ክፍል ያሳተማት ከ40 ገጽ የማትበልጥ መጽሐፊት ናት። ሌላ የተጻፈ ካለ አላውቅም። ይህ መጣጥፍ ወደፊት ለሚጽፉ ጸሐፊዎች ወይም ይህን ሊያስፋፉ ለሚወዱ ቢጋር በመሆን ሊያገለግል ይችላል።




በመጀመሪያ በርእሱ የሚገኙትን ሁለት ጽንሰ አሳቦች (ራስታ እና እምነት ወይም ሃይማኖት) በአጭር በመፍታት እሻለሁ። ራስታ፥ ራስታፋሪ፥ ራስታፋሪያን (ራስ ተፈሪያውያን) በመባል የሚታወቁት ሰዎች በመጀመሪያና በአብዛኛው በጃሜይካ የሚኖሩ ጥቁሮች ናቸው። ሲጀመር ሁሉም ማለት ይቻላል የዝቅተኛ መደብ ክፍልና የችግረኛ ኑሮ ተጋሪዎች ነበሩ። በአሁኑ ጊዜ የራስታዎች ኅልውና የዚያን አንድ አገር አንድ መደብ ብቻ ሳይሆን አገሮችን ያካለለ ከአሜሪካ እስከ አውሮጳ፥ እስከ ጃፓን እስከ በርካታ የአፍሪቃ አገሮች በተለይም ኢትዮጵያ የዘመተ ክስተት ሆኖአል። ጥቁሮችን ብቻ ሳይሆን የአውሮጳም የእስያም ዝርያዎችንና የጥቁር ዲቃላዎችንም ያቀፈ ሆኖአል። የቀለም ድንበርን በመጣስ ሌሎችንም መሳብና መዋጥ የጀመረ ሁኔታም ነው። ለምሳሌ በጃፓን የጃፓን ራስታዎች የሚባል ጎራ ይገኛል።

## ንቅናቄ ወይስ ሃይማኖት?

ሁለተኛው ነጥብ ራስታፋሪያኒዝም እንቅስቃሴ ወይም ንቅናቄ ነው ወይስ ሃይማኖት? ራስታዎች እንደ ሃይማኖት እንጂ እንደ ንቅናቄ ወይም ፍልስፍና እንዲታዩና መታወቅን አይፈልጉም። ኢዝም የሚል ቅጥያ ስላለበት ራስታፋሪያኒዝም የሚለውን መጠሪያም አይወዱትም። የማይወዱበት ምክንያትም የ 'ኢዝም' ቅጥያዎች፥ ለምሳሌ፥ (Humanism, Marxism, Agnosticism) የፖለቲካ፥ የማኅበራዊ፥ ወይም የትምህርታዊ እንቅስቃሴዎች መጠሪያ ናቸው እኛ ግን አይደለንም የሚሰኝ አቋም ነው።[1] ወደ ጅማሬያቸው ታሪክ ስንዘልቅ ግን የሃይማኖት መልክ ከመያዙ አስቀድሞ ፖለቲካዊም፥ ማኅበራዊም አቋም የነበረው የአርነት ወይም ከፊል አርነት ንቅናቄ እንደሆነ እንረዳለን። እንዲያውም ሃይማኖታዊ መልክ የያዘው ንቅናቄነቱ አልሰምር ስላለው ይመስላል። ይህ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ነው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ፖለቲካዊ ክንፉ እንደገና እየተራገበ ያለ ይመስላል። ለምሳሌ በ2001 የመጀመሪያው የራስታ ፖለቲካዊ ፓርቲ ተመሥርቶ ለውድድር ቀርቦ ነበር። በ2002 ደግሞ የኃይለ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አባላት Imperial Ethiopian World Federation Incorporated Political Party IEWFIPP የሚባል ፓርቲ መሠረቱ። ችግሩ ብዙዎቹ ራስታዎች ንቁ የፖለቲካ ተሳታፊዎች አይደሉምና የድጋፍ መሠረቱ ጠንካራ አይደለም። እንግዲህ ሲደመደም ራስታፋሪያኒዝም በአርነት ናፍቆትና አፍሪቃዊ ስነ ልቡና የተጸነሰ ንቅናቄም የክርስትናና የጥቁር አይሁዳዊነት ቅይጥ የሆነ ሃይማኖትም ነው ማለት ይቻላል። ሁለቱም ነው።

ንቅናቄነቱ በመጀመሪያ በነጭ ጥላቻና በጥቁርነት ስነ ልቡና ግንባታ ያተኮረ ሆኖ የጃሜይካ ሰዎችም ሆኑ የካሪቢያን አገሮችና የአሜሪካም ጥቁሮች ሁሉ ወደ አፍሪቃ በተለይም ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ ጥሪት ያደረገ ነበረ። ወደ ኢትዮጵያ የገቡቱ በርካታ ቢሆኑም መግባታቸው ብቻ ሳይሆን በአሁኑ ጊዜ ያሉትም ቁጥራቸው የመነመነ ነው። ይሁን እንጂ ሃይማኖቱ

---

[1] በዚህ መጣጥፍ ውስጥ "ራስታ" የሚለውን ቃል ስጠቀም የሃይማኖቱንም ሆነ የንቅናቄውን ጠቅላላ ገጽታ መቃኘቴ ነው።

ከመመንመን ይልቅ እየተስፋፋ እንደሚገኝ ይታያል። በተለይም በኢትዮጵያም ሆነ በሌላውም ዓለም ወደ ራስታ ሃይማኖት የሚገቡቱ ከክርስትና እምነት መሆኑ ይዘገባል። እነዚህ የስም ብቻ ክርስቲያኖች ወይም መጽሐፍ ቅዱስን የማያውቁ ወይም የማያነብቡ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ሆኖም ‘ቀድሞ ክርስቲያን ነበርኩ’ ባዮች ናቸው። በአሁኑ ጊዜ ጃሜይካን ጨምሮ በዓለም ላይ ከ0.6-1ሚሊዮን የሚደርሱ ራስታዎች እንዳሉ ይገመታል። ይህ ቁጥር በጣም የተጋነነ ሆኖም ይገመታል። የጃሜይካ እስታቲስቲክስ የሚያሳየው የጃሜይካ ራስታዎች ከ25-30 ሺህ እንደሚሆኑ ነው፤ ይህም ከአገሪቱ ሕዝብ ከ2% ያነሰ ነው ማለት ነው።

## ማርከስ ጋርቪና የጥቁርነት ስነ ልቡና

እንደ ራስታዎች ቀዳሚ ነቢይ (በአንዳንዶቹ ዘንድ እንደ መጥምቁ ዮሐንስም በመመሰል) የሚቆጠረው ማርከስ ጋርቪ በ19 አስራዎቹ ውስጥ (ራስ ተፈሪ ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴና አልጋ ወራሽ ሳሉ) ‘በአፍሪቃ ጥቁር ንጉሥ ሲነግስ መዳን ይሆንልናል ወደ አፍሪቃ ተመልከቱ’ የሚል ንግርት በማውራት ጥቁሮችን ያደፋፍርና ያስተባብር ነበር። አልጋ ወራሽና በኋላ ንጉሥ ተፈሪ የነበሩት ኃይለ ሥላሴ ተብለው ከጥቂት ዓመታት በኋላ ሥርዓተ ንግሥ ሲፈጽሙ ትንቢቱ እንደተፈጸመለት ነቢይ ተቆጠረ።



ማርከስ የጃሜይካ ተወላጅና “ወደ አፍሪቃ መመለስ” የሚለውን አስተሳሰብ የጀመረ ሰው ነው። ስሙ የሚጠራው የተባበሩት ጥቁሮች የመሻሻል ማኅበር (United Negro Improvement Association) የሚባለውን ማኅበር በ1916[2] በአሜሪካ በመመሥረቱ ነው። ከዚህ በፊት ለጥቁሮች መብት የሚሚገቱ ድርጅቶች ጥቂትና ደካማ ነበሩ።

ጃሜይካ የእንግሊዝ ቅኝ ሆና ለ300 ዓመታት ቆይታ እንደ ብዙዎቹ የአፍሪቃ አገሮች ነፃነቷን ያገኘችው በ1960ዎቹ ውስጥ ነው። ታዲያ ማርከስ በአሜሪካ ለ10 ዓመታት ከቆየና እንግሊዝን ከጎበኘ በኋላ የጥቁሮችን ኑሮና የባርነት ስነ ልቡና ተመልክቶ መፍትሔው ሰላምና ፍቅር፥ አንድነትም ባለባት አፍሪቃ ተመልሶ በመኖር ብቻ መሆኑን ሰበከ። ለነገሩ በዚያን ጊዜ ከኢትዮጵያ በቀር አፍሪቃ የአውሮጳ ቅርጫ ነበረችና የእግር ማረፊያ የላቸውም። ኢትዮጵያ ግን እንደ ተስፋ አገር የምትታይ ነበረችና የንቅናቄው ተከታዮች የተስፋ አገር ሆነች። በኋላ ንቅናቄው ሃይማኖታዊ ቅኝቱን ሲያቃና ኢትዮጵያ ጽዮን ጥቁሮችም 12ቱ ነገደ እስራኤል ሆነው አረፉት።

ማርከስ አወዛጋቢ በሆነ የአክሲዮን ክስ በአሜሪካ መንግሥት ለፍርድ ቀርቦ 5 ዓመት ታስሮ ፍርዱ ከማለቁ በፊት በአመክሮ ተፈትቶ ወደ አገሩ ወደ ጃሜይካ ሲመለስ ደማቅ አቀባበል ተደርጎለታል። ከ1935 እስከሞተበት እስከ 1940 የኖረው እንግሊዝ አገር ሲሆን በጊዜው በኢጣልያ በመወረር ላይ ስላለችው ኢትዮጵያ ሁኔታ በቅርበት ይከታተል ነበር። ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በጦርነቱ አገሪቱን ጥለው መውጣታቸውን በግልጽ መንቀፉ ይነገራል። ማርከስ የሃይማኖት ሰባኪ ሳይሆን ፖለቲኛና ማኅበራዊ መሻሻል ላይ የሚያተኩር ሰው ነው። በኋላ የሚጠቀሰው የራስታ መጽሐፍ ቅዱስ ደራሲ ሮበርት አትሊ ነቢይ ብሎ ሾሞት ነበር። ጋርቪ ግን፥ “እኔ ሃይማኖት ለማስተማር ጊዜ የለኝም” ብሎ ሲመልስለት ከነቢይነቱ መልሶ ሽሮታል።[3]

## የሃይማኖቱ እድገት

ከ18መቶዎቹ መጨረሻ ጀምሮ በጃሜይካ ሃይማኖታዊ፥ ማኅበራዊ፥ ለነፃነት የመቆምና የአርነት ንቅናቄዎች ተደባልቀው በሕዝቡ የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ሰርጸዋል። ስለዚህ የማርከስ ጋርቪ ፍልስፍና ወይም ትምህርት አዲስ ሳይሆን ቀድሞ በተቀደደ ፈር የሄደ ትልም ነው። ይሁን እንጂ ጋርቪ ለንቅናቄው፥ በተለይም በጃሜይካዊነቱ ለራስታዎች የመጀመሪያ አካሄድ ቅርጽ የሰጠና የፊት ቀስት ያሆነ ሰው ነው ተብሎ ይታመናል።

በ1930ዎቹ በጃሜይካ ራስታዎች ዘንድ ሃይማኖቱ ይህ የሚባል ግልጽ ቅርጽና አስተምህሮ እንዲሁም እገሌ የሚባል ታዋቂ መሪ ባይኖረውም እያደገ ሄዶአል። ሊዮናርድ ሃዌል የተባለው ሰው እንደ መጀመሪያው ሰባኪ፥ አስተማሪና መሪ ይታይ የነበረ የመጀመሪያዎቹን የሃይማኖቱን የአስተምህሮ መሠረት ያነጠፈ ሰው ነው። ይሁን እንጂ ይህ ሃዌል ንቅናቄውም ሆነ ራሱም ከፖሊስና ከመንግሥት ጋር በነበሩት ግጭቶች ሊታሰር በቃ። ከዚህ የተነሣና ከዚህ በኋላ ራስታዎች መሪ የሚሆን ሰው አልኖራቸውም፤ እንዲኖራቸውም አልፈለጉም። ሃዌል እንዲታሰር ያደረጉትን እንቅስቃሴዎች ከፈጠሩት ትምህርቶቹና ስብከቶቹ መካከል ጥቁር ከምንም ዘር ይልቅ የበላይ እንደሆነ ማመን፥ የነጭ ዘርን አጥብቆ

---

[2] የዘመን አቆጣጠሮች እንደ አውሮጳ ናቸው።

[3] *Holy Piby p. 54.*



www.Ethiocross.com

መጥላት፥ የነጭን ዘር በጥቁሮች ላይ ስለፈጸሙት በደል መበቀል፥ ባቢሎን ብለው የሚጠሩትን መንግሥትንና የሕግ ተቋማትን መቃወም፥ ማዋረድና ማሳደድ ይገኙበታል። ሌሎቹ፥ ማለትም ኃይለ ሥላሴን ማምለክና ወደ አፍሪቃ መመለስ ያን ያህል ችግር ፈጣሪ ባይሆኑም ከመጀመሪያ ትምህርቶቹ ውስጥ ይገኛሉ።

በዚህ ጊዜ ሦስት የተለያዩ ቡድኖች ነበሩት። እነዚህ ቡድኖች በኋላ ቤተ-ራስታ (Mansions of Rastafari) የሚባሉትን የሆኑት ናቸው። እነዚህ ቤተ-ራስታዎች ኒያቢንጊ (የአርነት ተዋጊ)፥ ቦቦ ሻንቲ ወይም ቦቦ አሻንቲ (ጥቁር)፥ እና 12ቱ ቤተ እስራኤል የተባሉት ናቸው። ሁሉም ቡድኖች በአንድነት የሚያምኑበት እምነት አላቸው። ይህ የጋራ መልክ ቅኝ አገዛዝን ማውገዝ፥ ወደ አፍሪቃ መመለስ፥ ሰላማዊ (ትጥቅ-አልባ) ተቃውሞ ማድረግ፥ እና ኃይለ ሥላሴን ማምለክ ናቸው። ሆኖም የጎላ መሪ አልነበራቸውም። በሦስቱ ቡድኖች ወይም ቤተ ራስታዎች መካከል መመሳሰል እንዳለ ሁሉ መጠነኛ ልዩነቶችም አሉ።

ኒያቢንጊዎች ስማቸውን የሰየሙት በ19ኛው ምዕተ ዓመት ውስጥ በነበረችው የዩጋንዳ ንግሥት ነው። ይህች ሴት ቅኝ አገዛዝን የተፋለመችና ለሌሎችም ሁነኛ ምሳሌ ናት ብለው በማመን ስማቸውን ኒያቢንጊ ብለው ጠሩ። ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ጃሜይካን በጎበኙ ቀን ይህ ቡድን በእጅግ ቁጥርና በትልቅ ቅስትና መፈክር ንጉሡን የተቀበለ ቡድን ነው። ይህ ቡድን የመጀመሪያው ሲሆን ሌሎቹ ከዚህ የወጡ ናቸው። የዚህ ቡድን ዋና መታወቂያ የራስ ተፈሪ በሥጋ የተገለጠ አምላክነት እና የጥቁሮች ሁሉ ምንጭ ወደ ሆነችው ወደ ኢትዮጵያ መመለስን ማጽናት ናቸው።

ቦቦ ሻንቲዎች ራስን በመቻል፥ በማኅበር በመኖር፥ የእጅ ሙያዎችን ውጤቶች ለምሳሌ፥ የባህል ባርኔጣዎችን ሠርቶ በመሸጥ የሚተዳደሩ ናቸው። ጋንጃ ወይም ዕጽ በአደባባይ ማጤስን ያወግዛሉ። የዚህ ምክንያት ጋንጃ መጤስ ያለበት በአምልኮ ሥርዓት ብቻ ነው ብለው ስለሚያምኑ ነው።



12ቱ ነገደ እስራኤል የሚሰኘው ቡድን ወይም ቤተ ራስታ ከአገሪቱ ነፃነት በኋላ በ1960ዎቹ መጨረሻ ነቢዩ ጋድ በሚሉት ዶክተር ቨርነን ኬሪንግተን የተመሰረተ ነው። ይህ ቡድን ከሌሎቹ ከሁለቱ ለዘብተኛ የሆነ ቡድን ነው። የዚህ ቡድን ሰዎች በቤታቸው ውስጥ ወይም በሚመስላቸው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማምለክ ይችላሉ። እነዚህ ከ12ቱ የየትኛው ነገድ ትተወላጅ መሆናቸውን የሚያውቁት በሚወለዱበት ወር ነው። በጥር የተወለዱ የንፍታሌም፥ የካቲት የዮሴፍ፥ ሐምሌ የይሁዳ (ኃይለ ሥላሴ በሐምሌ ወር ስለተወለዱ መሆን አለበት)፥ ነሐሴ የይሳኮር ወዘተ ነው። ያልሆኑትን ለመሆን ከመሞከራቸው ግራ የገባው የነገድ አመራረጥ አላቸው። ለምሳሌ አባትየው በመስከረም ተወልዶ የዛብሎን ነገድ ቢሆን ልጅየው በታኅሣስ ቢወለድ እንደ አባትየው የዛብሎን ነገድ ሳይሆን የአሴር ነገድ ይሆናል ማለት ነው። ይህ ጨዋታ ነው። ነቢዩ ጋድ 12ቱን ነገዶች በወራት ብቻ ሳይሆን በቀለምና በሰውነት ብልትም (የኀፍረተ ሥጋ ብልት ሳይቀር) ይከፋፍላቸዋል። የሚያፌዝ መሆኑ ግልጽ ነው፤ ግን የሚለውን ሁሉ እውነት ነው ብለው የሚቀበሉ መኖራቸውም እውነት ነው።

ከላይ እንደተጠቀሰው በመጀመሪያዎቹ የእድገታቸው ዓመታት ይህ ያልተደራጀ እንቅስቃሴያቸው በ2ኛው የዓለም ጦርነትና በኢኮኖሚ ቀውስ ምክንያት ከሰላማዊ ተቃውሞ ወደ ግጭት አለፈ። ይህ ለቅኝ ገዥው መንግሥት አስቸጋሪ ክስተት ነበር፤ በርካታ ራስታዎች ከፖሊስ ኃይል ጋር በመጋጨት ታስረዋል ተገድለዋልም። ይሁን እንጂ በነዚህ ዓመታትና እስከ ነፃነት ድረስም በገሃድ 'ይህ እምነታችን ነው፤ ይህ ቅዱስ መጽሐፋችን ነው፤ ይህ የአምልኮ ሥርዓታችን ነው' የሚባል ግልጽ ሰነድ አልነበራቸውም። የላላ ግንኙነትና የጥቁርነት ስነ ልቡና ያያያዛቸው ቡድኖች ነበሩ።

አምልኮአቸውም አንድ ወጥ ሳይሆን እንደ ቡድኑ ዝንጉርጉር ነው። ሆኖም ቀደም ሲል በተጠቀሱት ዋና ዋና የእምነት ነጥቦች ይቆራኛሉ። በኋላ ላይ ሃይማኖቱ እንደ ዋና ዋና አንቀጾች የሚታወቁ ሰነዶችና ስነ መለኮት፥ የሃይማኖቱ በዓላት፣ እንዲሁም ቅዱሳት መጻሕፍት ኖሮታል።

## የራስታዎች መጻሕፍት

ሀ) የመጀመሪያውና የራስታዎች 'መጽሐፍ ቅዱስ' የሚሰኘው በቋንቋቸው ሆሊ ፒቢ (Holy Piby) የሚሉት መጽሐፍ ነው። ሆሊ ፒቢ በመቅድሙ የመጀመሪያ ቃል መጽሐፉ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ለኢትዮጵያ ዘሮች ሁሉ ደኅንነት ስለ መጻፉ እንዲህ ይላል፥ The Holy Piby, a book founded by the Holy Spirit to deliver the gospel commanded by the Almighty God for the full salvation of Ethiopia's posterities. ይህ በ1924 በራብርት አትሊ ራጀርስ የተጻፈውና በኑዋርክ፥ ኒው ጀርዚ (አሜሪካ) የታተመው ከ100 ገጽ ብዙ የማይበልጥ ትንሽ መጽሐፍ አትሊ ለመሠረተው የአትሊካን ቤተ ክርስቲያን መገልገያነት የጻፈው ነው። አትሊይ ይህን አዲስ የጥቁሮች ሃይማኖት አትሊካኒቲ (Athlicanity) ሲለው ቤተ ክርስቲያኑም አፍሮ አትሊካን

ግንባታ ቤተ ክርስቲያን (Afro Athlican Constructive Church) የሚባል ነበር።

ይህ መጽሐፍ በአመነጫጨቱ [ባለፈው ስለ ሞርመኖች ከጻፍኩት ጋር ይቀራረባል] ዳግላስ የሚባል መልአክ ለአትሊ የገለጠለት ኪዳን ነው። ከብሉይ ኪዳን የሚፈልጋቸው ጥቂት አሳቦች ወስዶ፥ እንደሚያመቸው ለውጦ፥ የራሱን የጥቁር ጭቆና ያመረተውን አስተሳሰብ ጨምሮ፥ ቀያይጦና ኢትዮጵያዊነትን ከልሶበት ያበሰለው መጽሐፍ ነው። የአጻጻፉ ስልት የዮሐንስ ራእዩን አይቶ የጻፈበት ዓይነት ነው። ራስታዎች ኢትዮጵያ የሚለው ቃል የሚጠቀሙት በኢትዮጵያ ያሉትን ብቻ ሳይሆን ራሳቸውንና ጥቁሮችን ሁሉ በመወከል ነው።




መልአኩ ዳግላስ ለአትሊ 12ቱን ትእዛዛት ሰጥቶትም ነበር። እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው አሥር ሲሆን ይህ 12 እና ለኢትዮጵያ ዝርያዎች ነው። ከዐሥርቱ ትእዛዛት የመጀመሪያውን የሚመስለው ብቻ በ12ኛው በስሱ ሲጠቀስ የተቀሩትን በራሴ ቃል ሳጠቃልላቸው፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ፥ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፥ ሠራተኞች፥ ቆጣቢዎች ሁኑ፥ አንድነት ይኑራችሁ፥ የሌላውን ሕዝብ ጭቆና አቅልሉ፥ መላእክት አብረዋችሁ ስለሚኖሩ ንጹህና ደስተኞች ሁኑ፥ ሰዓት አክባሪዎችና ታማኞች ሁኑ፥ ወዘተ የሚሉ ናቸው። ይህ ነው ሙሴ ለእስራኤል እንደሰጠው ትእዛዛት ተደርጎ የሚቆጠረው። ይህ ብቻውን የሆነ አንድ አምላክን ማምለክንና በቅድስና ለእርሱ እየተገዙ መኖርን ሳይሆን ማኅበራዊ ተሃድሶን የሚያመላክት ስብከት ነው።

በአንድ ጉባኤ ውስጥ አንድ አዲስ የአትሊ ተከታይ ሰው አትሊን፥ "ብፁዕ ሆይ የአትሊካዊ ሃይማኖት ዋና እምነት ምንድርነው?" ብሎ ሲጠይቅ የተሰጠው መልስ፥ "the fundamental belief of the Athlican faith is justice to all" ብሎ ነበር።[4] በወቅቱ ጥቁሮች እያለፉ ያሉበትን ጭቆና ማስተዋል ይህን ሃይማኖት ሃይማኖት ሳይሆን ሃይማኖትን የተቀባ የአርነት ትግል ብሎ መደምደም ያስችላል። በዘመኑ ታዋቂ የሆነውን የጥቁር መብት ተሟጋች ማርከስ ጋርቪን በአንድ ምዕራፍ ውስጥ ያወድሰዋል። ሆሊ ፒቢ ጸሐፊውን ከፍ ለማድረግና ለማሠልጣን እርሱ የመሠረተውን ማኅበርም ለመግዛት የተጻፈ መጽሐፍ ነው። ከመጽሐፍ

______________________________

[4] *Holy Piby p. 50.*

ቅዱስ በደፈናው ጀርባና ጀርባ ናቸው ብሎ የሚደመደም መጽሐፍ ነው። የመጽሐፉ ደራሲና የማኅበሩ መሪ አትሊ ሮጀርስ በ1931 ራሱን የገደለ ሰው ነው። ሆሊ ፒቢ ወይም በአንዳንዶች ዘንድ 'የጥቁሮች መጽሐፍ ቅዱስ' የሚባለው ይህ መጽሐፍ ከታተመ በኋላ በራስታዎች ዘንድ ወዲያውኑ ተቀባይነትን ያገኘ መጽሐፍ ሆነ።

ለ) ራስታዎች መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ቅዱስ መጽሐፍ በከፊል ይቀበሉታል። በተለይም King James Version የተባለውን በ1611 የታተመ የእንግሊዝኛ ትርጉም ቢቀበሉትም በክርስትናም ሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያላቸው የተጀቦነ አመለካከታቸው ባቢሎናዊው ሥርዓት ለራሱ ጥቅም ሲል በርዞታል ይላሉ። ራስታዎች ባቢሎን ወይም ባቢሎናዊ ሥርዓት የሚሉት በመጀመሪያ የጃሜይካን አገዛዝ ቢሆንም አውሮጳንና አሜሪካን ያማከለና ነጭንና ሥርዓቱን ያገዘፈ ማናቸውም ማኅበራዊ፥ ምጣኔ ኃብታዊ፥ ሃይማኖታዊ፥ ፖለቲካዊ ሥርዓት ሁሉ ነው። ይህ ባቢሎናዊ ሥርዓት መጽሐፍ ቅዱስንም ለነጭ የበላይነት አውሎታል የሚል ግምት አላቸው። ስለዚህ በርካታ ምንባቦችንና ትንቢቶችን ለኢትዮጵያና ለራስ ተፈሪ እንደተነገሩ አድርገው ይተረጉማሉ። ራስታዎች ይህን መጽሐፍ ቅዱስ በጣም እንደሚያነብቡት ቢነገርም መጽሐፍ ቅዱስን እንደ መጽሐፍ ቅዱስነቱ ወይም እንደ እግዚአብሔር ቃልነቱ ሳይሆን የሚፈልጉትን ብቻ በመልቀም ስልት ስለሚያነብቡት በፊታቸው ያለውን እውነት ሳያዩት ያልፉሉ። ደግሞም መጽሐፍ ቅዱስ

ሐ) ክብረ ነገሥት በመጀመሪያ በቅብጥ ተጽፎ ወደ ዐረብኛ ከዚያም ወደ ግዕዝ እንዲሁም በቅርቡ ወደ አማርኛ የተተረጎመ መጽሐፍ ነው። የኢትዮጵያ ነገሥታት ምንጫቸውንና ስርወ መንግሥታቸውን ከሰሎሞንና ከንግሥት ማከዳ የሚጀምሩበት ታሪካዊ ሰነድ ተደርጎ የሚታይ መጽሐፍ ነው። የዚህ መጽሐፍ ምንጭና ግፊት አወዛጋቢ ቢሆንም ራስታዎች ስለ ኃይለ ሥላሴ የይሁዳ ዘርነት ማረጋገጫቸው አድርገው ይወስዱታል።

መ፥ሠ) ሌሎች ሁለት የሚቀራረቡ መጽሐፎች አሉ። የተስፋው ቁልፍ (The Promised Key) የራስታዎች የመጀመሪያ ካህን የሚሰኘው ሊዮናርድ ሃዌል የጻፈው መጽሐፍ ነው። በራሱ ስም ሳይሆን በአንድ የሂንዱ ሃይማኖት ጉሩ (አስተማሪ፥ ሊቅ እንደማለት ነው) ስም ያሳተመው ነው። አንዳንዶች ይህ መጽሐፍ ይህ መጽሐፍ በራሱ ስም ሳይሆን በብዕር ስም የታተመው የተኮረጀ በመሆኑና አኮራረጁም ለራስታዎች ሃይማኖትና ስነ ልቡና እንደሚመች ተደርጎ ነው ይላሉ። የተኮረጀውም አሁንም ራስታዎች ከመጽሐፎቻቸው እንደ አንዱ ከሚቆጥሩት ንጉሣዊው የጥቁር በላይነት ጥቅልል (የብራና መጽሐፍ እንደማለት ነው) (The Royal Parchment of Black Supremacy ) ከሚባለው ፊትዝ ባሊንቲን

ፒተርስበርግ የተባለ ጃሜይካዊ ካህን ከጻፈው መጽሐፍ ነው ይባላል። እነዚህን ሁለት መጽሐፎች ለማየት አላገኘኋቸውም፤ ስለ መጽሐፎቹ ከተጻፉ አስተዋጽዖዎች እንደተረዳሁት ግን ይህ በ1926 የታተመው መጽሐፍ የጥቁሮችን የበላይነት የሚያንጸባርቅና ጥቁሮች ቢያንስ አፍሪቃን ባማከለና ኢትዮጵያዊ ኩራትን በተላበሰ መልኩ የራስ ገዥነት መብት መጨበጥ እንዳለባቸው የሚያስተምር ነው። (የጥቁር የበላይነት ማለት በእኩልነት የማያምን የነጭ የበላይነት ተቃራኒ ንቅናቄ ነው። ከዚህ ትምህርት የተወለዱና ዛሬም በአሜሪካ የሚገኙ ነጭን ከጥቁር ያነሰ ዝቅተኛ ፍጡር አድርገው የሚያዩ የትላቻ ቡድኖች ይገኛሉ)።

እነዚህ አምስት መጻሕፍት የራስታዎች ሃይማኖት የሚያቅፋቸው መጻሕፍት ናቸው። ከክርስቲያን እይታ አንፃር ሲታይ መጽሐፍ ቅዱስን ከነዚህ መካከል ማስገባታቸው ግጭት ነው። እንደ መርጦ ለቃሚ ሃይማኖቶች (syncretism) ወይም እንደ ሠርገኛ ጤፍ ይሁን ካላሉ እርስ በርሱ የሚቀዋወም እምነትን እንዴት ማጣመር ይችላሉ? ከነዚህ መጻሕፍት መልከ ልንደመድም የምንችለው እንደ ሃይማኖት ከተወሰደ የራስታዎች ሃይማኖት የክርስትና የአይሁድ እና የጥቁርነት ጥልፍ ነው።

## ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በጃሜይካ

ራስታዎች ራስታ ተብለው የተጠሩበት መጠሪያ ምንጭ የራስ ተፈሪ መኮንን ስም ነው። ተፈሪ መኮንን የዐፄ ኃይለ ሥላሴ መጠሪያ ስም ነው። ንቅናቄውና ከንቅናቄ ወደ ሃይማኖት በአዝግሞት የተለወጠበትና የተዛወረበት ዘመን ከዐፄ ኃይለ ሥላሴ ሥርዓተ ንግሥ ቀደም ብሎ በነበረው ዐሥርት ነው።

በ1960ዎቹ ውስጥ ራስታዎች ጽዮን ወደሚሉአት ኢትዮጵያ መግባት ጀመሩ። በ1960 ራስታዎች አንድ ቡድን ወደ ተስፋዋ አገራቸው አፍሪቃ ሄዶ ጎብኝቶ እንዲመታ ላኩ። ይህ ቡድን መጥቶ አፍሪቃን ጎብኝቶ ከተመለሰ በኋላ ወደ አፍሪቃ ለመመለስ ጦዞ የነበረው የራስታዎች ምኞት በጣም ሟሸሸ። አፍሪቃ ያልሙት እንደነበረው ወተትና ማር የሚፈልቅባት የሰላም ምድር አለመሆኗን አዩ። ከዚህ ቡድን ጋር በተያያዘ በ1961 የራስታ ሽማግሌዎች ወይም መሪዎች ለንጉሡ ሠላምታ ለመስጠት (ለመሳለም) ወደ አዲስ አበባም መጥተው ነበር። ወደ ተስፋዋ አገር ቁንጮ ኢትዮጵያ የመምጣት ምኞታቸውም ንጉሡ በሻሸመኔ ከሚገኘው ርስታቸው ቆርሰው እንዲሰፍሩ ሲፈቅዱላቸው እውን ሆነ። የመጀመሪያው ሰፋሪ የሆነው ኖዌል ዳየር የተባለው ራስታ በ1965 መጥቶ ሲሰፍር ሌሎችም ተከተሉ። በአንድ ወቅት ከ2ሺህ በላይ ደርሰው ነበር።



ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ጃሜይካን በይፋ የጎበኙት April 21 1966 ነበር። በኋላ ይህ ቀን ከራስታዎች በዓላት አንዱ የሆነውና Grounation Day ተብሎ የተጠራው ነው። አውሮፕላኑ በማረፊያው ደርሶ ከቆመ በኋላ ሲወጡ አየሩ በጩኸትና በጋንጃ (እንደ ሲጋራ የሚጤስ ማሪዋና ወይም ካናቢ የሚባል አደንዛዥ ዕጽ) ሽታ ተሞልቶአል። ከአውሮፕላን ከመውጣት ወደ ውስጥ ተመልሰው 1 ሰዓት ቆዩ። ከ100 ሺህ በላይ ጃሜይካውያን (የሚበዙቱ ራስታዎች ናቸው) በማረፊያው ተገኝተው ነበርና ሁኔታው ለደኅንነትና ለጥበቃ አስተማማኝ አልነበረም። ሁኔታዎች ረገብ ባይሉም ወጥተው ወደተዘጋጀው መኪና ገብተው ወደ አቀባበሉ ስፍራ ሲሄዱ። የሕዝቡ ጩኸት እጅግ ነበረ። ሕዝቡ በጩኸት ድምጽ ከሚያሰማቸው መፈክሮች መካከል 'ጃህ (አምላክ) ራስታፋሪ'፥ 'የነገሥታት ንጉስ'፥ 'ሥላሴ ክርስቶስ ነው' የሚሉ ይገኙበታል። ከአውሮፕላን ወርደው በተነጠፈላቸው ቀይ ስጋጃ ላይ አለመሄዳቸው ብዙዎችን አስገርሞአል። ይህ ለምን እንደተደረገ ግልጽ አልሆነም። ምናልባት ከጥበቃ ጋር የተያያዘ እርምጃ ይሆን?

በተለምዶ በአገራችን 'ራስታዎች ዐፄ ኃይለ ሥላሴን እንደ አምላክ የሚያዩበት ምክንያት አገራቸው ዝናብ ጠፍቶ በዚያን ቀን የእርሳቸው አውሮፕላን ሲያርፍ ስለዘነበ ነው' የሚባለው ድጋፍ የሌለው አባባል ነው። ምክንያቱም ራስታዎች በዚህ ጊዜ ወደ 40 ዓመት የቆየ የራስ ተፈሪ አምልኮ ታሪክ አላቸው። ይህን ጊዜ ሁሉ ዐፄ ኃይለ ሥላሴን እንደ አምላክ፥ እንደ መሢሕ ሲያመልኩ ኖረዋል።

## ቀኃሥ ይህን እምነት እንዴት አዩት?

በጃሜይካ ጉብኝ ወቅት ከራስታዎች መሪዎች መካከል የተጠሩ ቀርበው ከንጉሡ እጅ የወርቅ ሜዳልያ ተቀብለዋል። ሆኖም ከንጉሡ ዘንድ በቀጥታና በወል ንጉሡ አምላክ ወይም መሢሕ ስላለመሆናቸው የተነገረ መግለጫ አልነበረም። ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በክርስትና እምነትና በኦርቶዶክስ ሥርዓት የኖሩ ናቸው። በጃሜይካው ጉብኝታቸው ወቅት ዐፄ ኃይለ ሥላሴ

ለራስታዎች ስለ እርሳቸው ሰው ብቻ መሆን ግን ያስደመጡት ንግግር አልነበረም።

ወደ አገር ከተመለሱ በኋላ አባ ይስሐቅ የተባሉ አቡን ልከው በጃሜይካ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እንድትመሠረትና የኢትዮጵያን ሥርዓትና ባህል እንዲያውቁ ጥረት አድርገዋል። ራስታዎች ይህን በጣም ቢወዱም በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ለመጠመቅ ከፈለጉ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ አምላክ መሆናቸውን መካድ ግዴታ ሲሆንባቸው ደግሞ ጠሉት።

በአንዳንድ ጋዜጣዊ ቃለ ምልልሶች በግልጽ የእምነታቸውን ምንነት ገልጠዋል። ለአንዳንድ ራስታዎችም ይህን ግልጽ ማድረጋቸውን አውስተዋል። ለምሳሌ የካናዳው ጋዜጠኛ ቢል መክኒል በ1967 ንጉሡ ካናዳን በጎበኙ ጊዜ ቃለ ምጠይቅ ሲያደርግላቸው ይህንኑ ጉዳይ አንስቶ እርሳቸውን የሚያመልኩ ሰዎች መኖራቸውንና ለዚህ የሚሰጡት አስተያየት ምን መሆኑን ጠይቆአቸው ነበር። (ድምፁን ለመስማት http://www.jamaicans.com/music/audio/rasta.wav ይጎብኙ። ጋዜጠኛው ሲጠይቅ የሳተባቸው ሁለት ነጥቦች አሉ፤ አንዱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች እርሳቸውን ማምለካቸውን ሲሆን ሁለተኛው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ያለው ቃል ነው) መልሳቸው እንደሚጠበቀው ግልጽ ነው። የመለሱት፥ “እንደዚህ ያለ ቃል ሰምቼአለሁ፤ አንዳንድ ራስተፈሪያውያንንም አግኝቻለሁ፤ እኔ ሰውና መዋቲ መሆኔን፥ ለቀጣዩ ትውልድም ቦታ ለቅቄ የምሄድ መሆኔንና ሰው ከአምላክ ሰረጸ የሚል ወይም እንዲህ የመሰለ ስሕተት እንዳይፈጽሙ በግልጽ ነግሬአቸዋለሁ” ብለው ነው።

በሌሎች አገሮችና በሌሎች መገናኛ ብዙኃን ያደረጉትን መግለጫ እርሳቸውን ሥጋ እንደለበሰ አምላክ የሚያምኑ ሰዎች ወዳሉበት አገር ሄደው ይህን አምላክ ያለመሆናቸውን ጉዳይ እዚያው እና በግልጽ አለመናገራቸው ጥፋት ነው። ምናልባት ሰሚዎቹን የሚያስቆጣና ችግር የሚፈጥር ስለሆነ ይሆን? የእርሳቸውን ሰው ብቻ መሆንና እነዚህተናግረው ኖሮ ቢሆን ከችግሩ ይልቅ ዋናው ችግር መፍትሔ ሊያገኝ ይችል ነበር።



የዐፄ ኃይለ ሥላሴን ሞት በተመለከተም በራስታዎች ዘንድ የተከፋፈሉና አመለካከቶች አሉ። አንዳንዶቹ ከቶ መሞታቸውን አያምኑም፤ ፈጽሞ አይቀበሉም፡ ‘ባቢሎናዊው ሥርዓት የፈጠረው የፈጠራ ወሬ ነው እንጂ ሌላም አይደለም’ ይላሉ። አሟሟታቸውና የመጀመሪያ ቀብራቸው ጭጋጋማ መሆን ለዚህ በር የከፈተ ቢሆንም የአጽማቸው እንደገና መቀበርም አመኔታ አላሳደረባቸውም። ወደ ሌላ ከፍ ወዳለ የማዕረግና የክብር ቦታ ተላለፉ እንጂ አልሞቱም ይላሉ። መሞታቸውን የሚቀበሉት ደግሞ መሞታቸው ምንም ለውጥ እንደማይፈጥርና በትንሣኤ መንፈስ ከእነርሱ ጋር መሆናቸውን ያወሳሉ። ስለዚህ ምንም እንኳ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ቢሞቱም አምልኮው እንዳልሞተ ይስተዋላል።

## ራስታዎችና ዘመናዊ መልካቸው

ራስታዎች እስከ 60ዎቹ መጨረሻ ድረስ በብዙዎች እይታ እንደ አፍራሽና አሉታዊ ኃይል ብቻ ይታዩ ነበር። በተለይ በ1968 በጃሜይካዊው የዩነቨርሲቲ አስተማሪ በዋልተር ሮድኒ የተጀመረው የጥቁር ኃይል ንቅናቄ (Black Power Movement) ራስታዎች በስፋት የገቡበት አክራሪ ግራ ክንፍ (ኮሚኒስታዊ መልክ ያለው) የፖለቲካ እንቅስቃሴ ነበረ። ይህ ንቅናቄ በበርካታ የካሪቢያ አገሮች መጉላቱ አሁንም የራስታዎችን መልክ በቀና እንዲታይ አላደረገውም። በ70ዎቹ ግን በአርት በተለይም በሬጌ ሙዚቃ በኩል አዎንታዊ የባህል ተጋቦት ማሳደር ጀመሩ።

ታዋቂው የሬጌ አቀንቃኝ ቦብ ማርሊ ከመሞቱ ቀደም ብሎ በጃሜይካዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክ በአቡኑ እጅ ቢጠመቅም በዘመኑ ሁሉ የራስታ ሃይማኖት አንድ ምልክት፥ እንዲያውም ከምልክቶቹ እንደ ቁንጮ ሆኖ ኖሮአል። እንዲያውም የራስታ ሃይማኖት እንዲታወቅ አዎንታዊው የባህል ተጋቦት ዋና መሣሪያ ነበረ።



ራስታዎች የክርስትና፥ የጥቁርነትና፥ የአይሁድ ሃይማኖቶች ቅይጥ ቢሆኑም ከሁሉም ጋር የሚጋጭ ማንነት ያላቸው ናቸው። መጽሐፍ ቅዱሳቸውን የማውቁ ሰዎች በትምህርት ነፋሳ በቀላሉ ሊወሰዱ እንደሚችሉ ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌ. 4፥14 ጽፎአል። ዛሬ ለአንዳንድ ወጣቶች ወደዚህ ጎራ ለመቅረብ መስህብ ከሚሆኑት ነገሮች መካከል የጎሉት የጌታን ቃልና የቃሉን ጌታ ካለማወቅ ቀጥሎ የሬጌ ዘፈኖች፥ የጋንጃ (ወይም ካናቢ የሚባል አደንዛዥ ዕጽ) ማጤስ፥ የጥቁር ወይም ጥቁርነት ስነ ልቡና፥ እና እንደ ፋሽን የሚታየው የድብዳብ ጠጉር (dreadlock) ናቸው።

የራስታዎች ጋንጃ ወይም ማሪዋና ማጤስ በአሜሪካና እንግሊዝን ጨምሮ በአንዳንድ የአውሮጳ አገሮች ከመንግሥት ጋር ያጋጫቸው ልማድ ነው።



ራስታዎች ይህን ከአምልኮ ጋር ቢያያይዙትም አደንዛዥ ዕጽ አደንዛዥ ነውና በአካልና በአእምሮ ላይ ችግር ማስከተሉ የማይቀር ነው። ከላይ በአማርኛ ስለራስታዎች በተጻፈው መጽሐፍ ውስጥ ይህ ችግር በኢትዮጵያም ከአስከፊ ገጽታዎች ጋር ተቆራኝቶ እየተከሰተ መሆኑ ተጽፎአል።

ራስታዎች በጃሜይካ ይጀምሩና ይስፋፉ እንጂ፥ ደግሞም ይህን ያህል ወደ ሚሊዮን የሚጠጋ በቀጥታም በተዘዋዋሪም ከሃይማኖታችን ጋር የተቆራኘ ሕዝብ አለ ይበሉ እንጂ በአገራቸው ሃይማኖታቸው ሕጋዊ ተቀባይነትን አላገኘም። ከፍርድ ቤት ውጪ (out-of-court agreement) ስምምነት በ2003 የአገሪቱ ፍርድ ቤት ለሃይማኖቱ ለመጀመሪያ ጊዜ እውቅና ቢሰጥም ራስታ እስረኞች በእስር ቤት ውስጥ በአምልኮ ምክንያት ጋንጃ እንዲያጤሱ ፈጽሞ አይፈቀድም።

## ስሕተቶችና ከቃሉ አንጻር

ራስታዎች ከጅምራቸው አንሥቶ መሪ የሌላቸውና ከተከፋፈሉ በኋላም የላላ ግንኙነት ያላቸው ስለሆኑ እምነታቸውና እምነታቸውን የሚገልጹባቸው መንገዶችም ግላዊ ዝንባሌ የሚታይባቸው ናቸው። በዚህ ክፍል ጥቂትና ጉልህ የንቅናቄውን/ሃይማኖቱን ስሕተቶች ከቃሉ አንጻር በማየት እደመድማለሁ።

1. የመጀመሪያው ነጥብ መነሻ መሆን ያለበት ቃሉ ነው። በግልጽ እንደሚታየው ራስታዎች መጽሐፍ ቅዱስን ሲጠቀሙ መራጮች ናቸው። ባቢሎናውያን የሚሉአቸው ነጮች መጽሐፍ ቅዱስን ወደ እንግሊዝኛ ሲተረጉሙ ያስቀሩት፥ የለወጡት፥ ያጣመሙት አለና መጽሐፍ ቅዱስን ስንቀበል ቅድመ ሁኔታ አስቀምጠን መሆን አለበት ባዮች ናቸው። ስናነብብም እነዚህን በባቢሎን የተወገዱ ነገሮች ለማስገባትና የገቡትን ለማስወጣት እየተጠነቀቅን መሆን አለበት ይላሉ። ደግሞም መጽሐፍ ቅዱስ ትንቢታዊና ምስጢራዊ ነው፤ ትንቢቱ ስለ ኃይለ ሥላሴ የተነገረ ምስጢሩም በፍለጋ የሚገኝ ነው ይላሉ።

በእውነቱ መጽሐፍ ቅዱስ ምስጢርና ምስጢሩም በፍለጋ የሚገኝ መጽሐፍ ሳይሆን፥ የእልፍ የማይገቡ አሳቦችና ትምህርቶች ጥርቅምም ሳይሆን ከብሉይ እስከ አዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያዘጋጀው የኃጢአት ስርየት መንገድ የተገለጠበት ግልጽ መጽሐፍ ነው። አንዳንድ ክፍሎች ከሌሎች ይልቅ ለመረዳት አዳጋች ሊሆኑ መቻላቸው፥ ምሳሌያዊ አነጋገሮችና ትንቢቶች ጊዜ የሚፈልግ ጥናት መጠየቃቸው እውነት ነው። ራስታዎች ለመጽሐፍ ቅዱስ ያላቸው አመለካከት የጥርጥር በመሆኑ የተጻፈውን ሁሉ አይቀበሉም ማለት ነው። የሚቀበሉት የመረጡትንና የፈለጉትን ብቻ ነው። ለምሳሌ ጋንጃ/ማሪዋና ለማጤሳቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ዘፍ. 1፥11-12፤ 3፥18 ወዘተ የሚገኘው ቡቃያ የሚል ቃል ነው። ማሪዋና ቡቃያ ነውና የተፈቀደ ነው ይላሉ። ለጠጉራቸው ድሪቶ መሆን የሚጠቅሱት እንደ ዘኁ. 6፥5፤ መሳ. 13፥5-16፥17 ወይም 1ሳሙ. 1፥11 ያሉት ጥቅሶች ናቸው። ልዩነቱንም አያስተውሉትም ናዝራውያን ለጊዜው የሚያሳድጉ ሲሆኑ እነዚህ ጠጉራቸው ተደብድቦ ለመኖሩም ጥቅስ አላቸው።

ራስታዎች የእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ የተበከለ ከመሰላቸው ውወደ ምንጩ ቋንቋ መሄድ ይገባቸው ነበር። እንዲህ የመሰለው ጠንካራ ፍለጋ በእነርሱ ዘንድ የማይታሰብ ነው። ችግራቸው ቃሉ መበከሉ ሳይሆን በሰይጣን ታውረው ቃሉን እንዳይቀበሉ የተቀለበሱ መሆናቸው ነው።

2. እግዚአብሔር ሉዓላዊ አምላክ ነው። ሉዓላዊ አምላክ ከሆነ አምላኪ የሆነ ሰው ታዛዥና ተገዢ ሊሆን ግዴታ አለበት። ራስታዎች ጃህ የሚሉት እግዚአብሔርን ይምሰል እንጂ ከቶም አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ከሁሉ በፊት የነበረ፥ ከሁሉ በላይ የሆነ፥ ፈቃዱን በቃሉ የገለጠ አምላክ መሆኑን በግልጥ ያወሳል። ስለ እግዚአብሔር ያላቸው አመለካከትና እምነትም ከምሥራቃውያን ሃይማኖቶች፥ ከአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ (New Age Movement) እና Pantheism / Panentheism አምላክ በሁሉም ውስጥ ሁሉም በአምላክ ውስጥ የሚል አመለካከት ጋር የተሳሰረ ነው። ስለዚህም ራሳቸውን ሲጠሩ ወይም እኔ ሲሉ 'እኔና እኔ' (I and I) ነው የሚሉት። አምላክ በሰው ሁሉ ውስጥ አለ፤ አንዱ እኔ እኔ ነኝ፤ ሌላው እኔ እርሱ ነው ማለታቸው ነው። አንዳንዶቹ I and I ሲሉ እነርሱንና ኃይለ ሥላሴን በኅብረት ማለታቸው ነው።

ራስታዎች አምላክ የሚሉት የጥቁርና የነጭ እየተባለ የሚከፈል ሲሆን ሰይጣን የነጮች አምላክ መሆኑን ያምናሉ። ሰይጣን የነጭ አምላክ ነው ሲሉ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰይጣን የተጻፈውን በመጣስ ማንነቱን መዘንጋታቸውና ለሽንገላው ወጥመድም ሰለባ መሆናቸው ነው።

3. መጽሐፍ ቅዱስ በወንጌላትና በአጠቃላይም በአዲስ ኪዳን የኃጢአታችን ስርየት የተፈጸመው በክርስቶስ የመስቀል ሥራ መሆኑን በማያዳግም ቋንቋ ይገልጣል። ራስታዎች ለክርስቶስ ስፍራ የላቸውም። ኃይለ ሥላሴ ከሙሴ፥ ከኤልያስ፥ እና ከኢየሱስ በኋላ የተገለጠው አራተኛው ሥጋ የለበሰ የመጨረሻው የጥቁሮች መሢሕ/ክርስቶስ/አምላክ ነው ይላሉ። የሚጠመቁትም በኃይለ ሥላሴ ስም ሲሆን በጃሜይካ ከምትገኘው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጋር ትልቁ ጠባቸውም በኃይለ ሥላሴ ስም አለመጠመቃቸው እና አባል ለመሆን ሲጠይቁ ራስ ተፈሪ መኮንን ወይም ዐፄ ኃይለ ሥላሴ አምላክ አለመሆኑን ተቀበሉ መባላቸው ነው። ስለዚህ እውነት፥ ሕይወትና መንገድ የሆነውን ጌታ ባለማወቅና ባለመቀበላቸው ደኅንነትን ወይም ከሞት ወደ ዘላለማዊ ሕይወት መሻገርን የማያውቁ ናቸው።

4. የነጭ ጥላቻና የጥቁር ግዝፈት አዲስ ኪዳን ከሚያስተምረው በክርስቶስ አንድ መሆን ጋር የተጣላ ነው። ፍቅር ከሆነውና ጠላትን ስንኳ መውደድን ያስተማረና የሚያስችል ክርስቶስ ከሌላቸው በጥላቻና በሞት ውስጥ መሆናቸው እውን ነው። አዲሱ ኪዳን የሚያስተምረን መጥላት ነፍስን ከመግደል እንደሚስተካከል ነው። ደግሞም አንድ ዘር ከሌላው እንደማይበልጥና እንደማያንስ ራስታዎች ለመረዳት አልጀመሩም። በቆየ ቂምና በጥላቻ፥ እንዲሁም ንቅናቄው በሚጀመርበት ዘመን በነበረው የተበላሸ ሥርዓትና አመለካከት አሁንም እንደታሰሩ ይገኛሉ።

5. ከአፍሪቃ በግድና በባሪያው ሥርዓት አስገዳጅነት በመምጣታቸው ወደመጡበት አገር ለመመለስ መናፈቅ አንድ ነገር ነው። አፍሪቃን/ኢትዮጵያን ጽዮን አሰኝቶ ከመጽሐፍ ቅዱስ መጥቀስና ማቆራኘት ግን ትክክል አይደለም። ጽዮን ኢትዮጵያ ወይም አፍሪቃ አይደለችም። ምድራዊቱ ጽዮን የዳዊት ከተማ ኢየሩሳሌም የተከተመችባት ኮረብታ ስትሆን ሰማያዊቱ ጽዮን ሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም ናት፤ ዕብ. 12፥22።

6. ራስታዎች የሃይማኖት ማኅበር ወይም ንቅናቄ እንጂ የእስራኤል ነገዶች አይደሉም። የእስራኤል ነገድነታቸው ምልክትም ጥቁርነት አይደለም። ሃይማኖቱን ተቀብሎ ወይም ንቅናቄውን ደግፎ ወደጎራው የሚገባ ነጭ ምን ሊባል ነው? ነገደ እስራኤል ወይስ ሌላ? መጽሐፍ ቅዱስን መርጦ አንባቢ ሆነው ክብረ ነገሥትን የሚቀበሉ ከሆነ ክብረ ነገሥት እንደሚናገረው የሳባ ንግሥት ከኢትዮጵያ ወይም አፍሪቃ ወደ እስራኤል መሄዷን ካወሳ ቀድሞም እስራኤልና አፍሪቃ የተለያዩ እንጂ አፍሪቃውያን ነገደ እስራኤል አለመሆናቸውን መቀበል ለምን ተሳናቸው?

ሲጠቃለል፥ ስለ ራስታዎች ስናስብ እንደሌሎች ደኅንነት እንደሚያስፈልጋቸው ሰዎች ሁሉ አዳኙ ክርስቶስ ኢየሱስ እንደሚያስፈልጋቸው እናስተውል። ራስታዎች ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያውያን ጋር ስሜታዊና ስነ ልቡናዊ ቁርኝት እንዳላቸው ስለሚያስቡ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ለነዚህ ሰዎች እውነታን ማሳየት የሚችሉ ጥሩ የወንጌል አብሳሪዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ እገምታለሁ። ብዙ ባይሆኑም አሁንም በሻሸመኔ አካባቢ ራስታዎች አሉ፤ ያመልካሉም።

በኢትዮጵያ የሚገኙ ራስታዎች እንዲያውም የቦብ ማርሊ አጽም ፈልሶ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ እንዲቀበር ጥረት እያደረጉ መሆናቸው በመግቢያው አንቀጽ በጻፍኩት መጽሐፍ ተጠቅሶ ይገኛል። 'ጃህ ያስተሰርያል' ን ጨምሮ የሬጌ የሙዚቃ ስልት ብቻ ሳይሆን የራስታ አስተምህሮም በዘመኑ ዘፋኞች አማካይነት በአድማጮችና በወጣቱ መካከል መናኘታቸው አቻ ምላሽ የሚጠይቅ ተግዳሮት ይመስለኛል።

ጸሎት የወንጌል ስርጭት ቃንጃ ነውና ራስታዎችን ካሉበት መንፈሳዊ እስራትና ጨለማ መውጣት እንዲችሉ መጸለይ ትልቅ አገልግሎት መሆኑን እናስተውል። አጋጣሚ ስናገኝም አይተናቸው 'ራስታዎች' ብቻ ብለን ከምናልፋቸው እውነተኛውን ከይሁዳ ነገድ ወደሆነው አንበሳ ወደ ክርስቶስ ኢየሱስን ልናቀርባቸው በቅንነት እንቅረባቸው።

እግዚአብሔር ከአርያም ይባርካችሁ። © ዕዝራ የስነ ጽሑፍ አገልግሎት / ዘመ

በሽተኛው

በሽተኛው ሐኪሙጋ ከወር በኋላ ሄዶ፥ "ዶክተር፥ ባለፈው ወር መጥቼ ካየሁህ ወዲህ ይኸው ምንም አልተሻለኝም" አለው።

"እንዴ! መድኃኒቱ ላይ የተጻፈውን አወሳሰዱን ልብ ብለህ አላነበብክም እንዴ?" አለው።

"እሱንማ አንብቤአለሁ ግን ከካርቶኑ ውስጥ ብልቃጡን አውጥቼ ሳነበው አጥብቃችሁ ገጥማችሁ ዝጉት ይላል። ታዲያ ሐኪሙ ዝጉት ያለውን እኔ እንዴት እከፍታለሁ ብዬ አልከፈትኩትም" አለና አረፈው።

ሁለቱ እብዶች

ሁለት እብዶች ከአማኑኤል ሆስፒታል ዘበኛውን አታልለው ለማምለጥ ይመካከራሉ። በምክራቸው መሰረት ወደመግቢያው ሲያመሩ ዘበኛው በቦታው የለም። "ዘበኛው ከሌለማ ማንን እናታልላለን?" ብለው እቅዳቸው ስለተበላሸ በመጥፋት ፋንታ ወደነበሩበት ተመለሱ።

'አባት'

አንድ አባት ዶክተሩጋ ይደውልና፥ "ዶክተር፥ ልጄ የቆርኪ መክፈቻውን ውጦታልና ቶሎ ድረስ" ይለዋል። ዶክተሩም፥ "ምንም አይሆን፤ ካመመው ነገ መጥቼ አየዋለሁ" አለው። አባትየውም፥ "እንዴ ዶክተር፥ እንግዶችኮ እየመጡ ናቸው፤ ለስላሳዎቹን በምን ልከፍት ነው?" አለው።

# ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች

በቀጣዮቹ የዕዝራ ስርጭቶች የፊልጵስዩስን መልእክት እንድናጠና እወዳለሁ። ይህ መልእክት ከሁለት ዓመታት በፊት በቤተ ክርስቲያናችን ያስተማርኩት ሲሆን አልፎ አልፎ በዕዝራ ውስጥ እጨምረዋለሁ።

በዚህ የመጀመሪያ ክፍል ከመልእክቱ በፊት የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን እንዴትና በምን ሁኔታ እንደተጀመረች በሐዋርያት ሥራ ከሚገኘው ክፍል እናያለን።

## መግቢያና የቤተ ክርስቲያኒቱ ዳራ

*ሐዋ. 15፥36-16፥40*

ለፊልጵስዩስ መልእክት ዳራ የሚሆነው ክፍል ሐዋ. 15፥36-16፥40 ያለው ነው። በሐዋ. 14 መጨረሻ የምናነብበው ጳውሎስና በርናባስ የመጀመሪያ ዙር የወንጌል አገልግሎታቸውን አጠናቅቀው ወደላከቻቸው ወደ አንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ተመልሰው የጌታን ሥራ ሲተርኩ ነው። 15፥26-28 እንዲህ ይላል፥ *ከዚያም ስለ ፈጸሙት ሥራ ለእግዚአብሔር ጸጋ አደራ ወደ ተሰጡበት ወደ አንጾኪያ በመርከብ ሄዱ። በደረሱም ጊዜ ቤተ ክርስቲያኑን ሰብስበው እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ያደረገውን ሁሉ ለአሕዛብም የሃይማኖትን ደጅ እንደ ከፈተላቸው ተናገሩ። ከደቀ መዛሙርትም ጋር አያሌ ቀን ተቀመጡ።*

የሾማቸው መንፈስ ቅዱስ ነው (ሐዋ.13፥1-4)፤ የላከቻቸው ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ናት። የወንጌል አገልጋዮች በሁለቱም ተጠያቂ፥ ለሁለቱን ተጠሪ ናቸው። እነጳውሎስ ሁለቱንም ይሰሙ ነበር፤ ለሁለቱም ታዛዦች ነበሩ። ሁለቱንም በመስማትና በመታዘዝ መካከል ምንም ግጭት አልነበረም። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ ሲመራት የምታደምጥና ምሪቱን የምትከተል ከሆነ በውሳኔዋ አትሳሳትም። በምሪት ካልሳተች በስምሪት አትስትም። የነጳውሎስ መመረጥና መላክ ከትክክለኛ ምሪት የመነጨ ትክክለኛ ስምሪት ነበረ። ይህ ለአገልጋዮች ጥሪና ሹመት እንዲሁም በመስክ መሰማራት አይነተኛ አካሄድ ነው።

> *እነጳውሎስ ለመንፈስ ቅዱስም ለቤተ ክርስቲያንም ተጠያቂም ተጠሪም ነበሩ። በምሪት ስህተት ካልኖረ በስምሪት ስህተት አይኖርም።*

በሐዋ. 15 መጨረሻ ደግሞ እነዚሁ ሁለት አገልጋዮች ለሁለተኛ ዙር ጉዞ ሲሰናዱ እናገኛለን። ከ36-41 ያለው ቃሉ እንዲህ ይላል፥ *ከጥቂት ቀንም በኋላ ጳውሎስ በርናባስን፥ ተመልሰን የጌታን ቃል በተናገርንበት በየከተማው ሁሉ ወንድሞችን እንጐብኛቸው፥ እንዴት እንዳሉም እንወቅ አለው። በርናባስም ማርቆስ የተባለውን ዮሐንስን ደግሞ ከእነርሱ ጋር ይወስድ ዘንድ አሰበ፤ ጳውሎስ ግን ይህን ከእነርሱ ጋር ሊወስድ አልፈቀደም፥ ከእነርሱ ዘንድ ከጵንፍልያ ተለይቶ ነበርና፥ ወደ ሥራም ከእነርሱ ጋር አልመጣም ነበርና። ስለዚህም እርስ በርሳቸው እስኪለያዩ ድረስ መከፋፋት ሆነ፥ በርናባስም ማርቆስን ይዞ በመርከብ ወደ ቆጵሮስ ሄደ። ጳውሎስ ግን ሲላስን መረጠ፥ ወንድሞችም ለእግዚአብሔር ጸጋ አደራ ከሰጡት በኋላ ወጣ፤ አብያተ ክርስቲያናትንም እያጸና በሶርያና በኪልቅያ ይዞር ነበር።*

በዚህ መሰናዶ የጉዞ ዝግጅት ብቻ ሳይሆን የአሳብ መለያየትም ይታያል። ጳውሎስና በርናባስ እንደ ማንም ሰው ሰዎችን የመገመትና የመመዘን የራሳቸው የሆነ ችሎታ አላቸው። አመራረጣቸውም ይህንን ችሎታቸውን የተደገፈ ነው። የበርናባስና የጳውሎስ መለያየት በአንድ ማርቆስ ወይም ዮሐንስ በተባለ ሰው ምክንያት ነው። ይህ [ምናልባት ወጣት የሆነ] ሰው አስቀድሞ ባደረጉት ጉዞ አብሮአቸው የነበረና በመካከል በማናውቀው ምክንያት ከጵንፍልያ ጀምሮ አገልግሎቱን አቋርጦ የተለያቸው ሰው ነው። ከጵንፍልያ በኋላ ብዙም ሳይቆዩ ነው ወደ አንጾኪያ የተመለሱት። ይህ አገልጋይ በሁለተኛው ዙር ጉዞ አብሮአቸው በመሄዱና ባለመሄዱ ምክንያት ነው የተካረረና መከፋፋትን የፈጠረ መለያየት በጳውሎስና በበርናባስ መካከል የሆነው።

ለአመራረጣቸው የየራሳቸው መለኪያ አላቸው። በርናባስ ሰዎችን ከላይኛው ቅርፊታቸው ዘልቆ መመልከት የሚችል ሰው ይመስላል። በችኮላና ባለማወቅ የተፈጸመ ስሕተትንና ጥፋትን የሚያልፍ ተፈጥሮ ያለው ሰው ይመስላል። ኃጢአትን ይቅር የማለትና ለጥፋተኞች ዳግም እድል መስጠት የሚያስደስተው ሰው ይመስላል። ሰዎችን ሲያይ እነርሱን ብቻ ሳይሆን በእነርሱ አማካይነት የሚሠራውን የወደፊት ውጤትም የሚያተኩር ሰው ይመስላል። ምናልባትም ማርቆስ ዘመዱ ስለሆነ (በርናባስ የማርቆስ አጎት ነው) አድልቶ አቅፎት ይሆን? እንዳልሆነ የሚያስረዱን ነገሮች አሉ። አንደኛው ከላይ ያየናቸው የበርናባስ ተፈጥሮ ነው። ጳውሎስን ራሱን አስቀድሞ ወደ ሐዋርያት፥ ኋላም ወደ አንጾኪያ ማን አመጣው? በርናባስ ነው። ለክርስቲያኖች ሁሉ ማስፈራሮ የነበረውን ጳውሎስን ወደ ወገኖች እንዲደባለቅ ድልድይ የሆነለት ሰው በርናባስ ነው። በርናባስ ጳውሎስን ነጠላውን ሳይሆን ጳውሎስን ወንጌላዊውን፥ መጋቢውን፥ አስተማሪውን፥ ሐዋርያውን ነበር ያየው። አንዳንድ ሰዎች በዛፍ ላይ የተንጠለጠለ ፍሬ ብቻ ያያሉ፤ አስተዋዮች ግን በፍሬ ውስጥ ያለውን ዛፍ ያያሉ። በርናባስ ይህ ሰው ነው። ሁለተኛው ደግሞ የራሱ የማርቆስ ተፈትኖ ብቁ ሆኖ መገኘት ነው። ይህንን በሚቀጥለው አንቀጽ እናያለን።

ጳውሎስ ግን እንዲህ አይደለም። አቋሙ ፈጣንና ቆራጥ ይመስላል። የማያወላውልና ሰዎችም እንዳያወላውሉ የሚፈልግ ይመስላል። በተለይም በክርስቶስ ወንጌል ምክንያት በሚመጣ ነገር ጀርባ መስጠን አይፈልግም። ሌሎችም ያንን እንዲሆኑ ይፈልጋል። ስለዚህ በማርቆስ ላይ አቋሙን ሲቆርጥ ይታያል። ይህ ማርቆስ ኋላ የተፈተነ አገልጋይ መሆኑንና ከጳውሎስ ጋርም በአገልግሎትም በእስርም አብሮ የነበረ መሆኑ በቆላ. 4፥10-11፤ 2ጢሞ. 4፥11፤ ፊልሞ. 24 ተጽፎአል። ከጴጥሮስም ጋር ስለማገልገሉ 1ጴጥ. 5፥13 ያሳውቀናል።

ከሐዋርያት ሥራ ታሪክ እንደምንረዳው ጳውሎስና በርናባስ በማርቆስ ምክንያት በአሳብና በተሰማሩበት በመስክ ቢለያዩም በዓላማቸው ግን አልተለያዩም። በርናባስ ከማርቆስ ጋር ወደ ቆጵሮስ፥ ጳውሎስም ሲላስን መርጦ ወደ ሶርያና ኪልቅያ ሄዱ። ከዚህ በኋላ ያለው የሐዋርያት ሥራ ታሪክ የጳውሎስን አገልግሎት የተከተለ በመሆኑ የበርናባስ አገልግሎት አልተጻፈልንም። ይሁን እንጂ ሁለቱም በወንጌል ሥራ ነበር የተሰማሩት። በአሳብ መለያየታቸው በዓላማ አልለያያቸውም። ክርስቲያኖች በአሳብ ሙሉ በሙሉ ላይስማሙ ይችላሉ፤ የአሳብ አለመስማማት ግን ዋናውን ዓላማ፥ የጌታን ክብርና የወንጌልን ሥራ ሊከለክል አይገባም። የነጳውሎስ ሕይወትና የአገልግሎት እርምጃ ይህን ያስተምረናል።

> *በአሳብ አለመስማማት ማለት በዓላማ መለያየት አይደለም። ጳውሎስና በርናባስ በአሳብና በምርጫ ባይስማሙም በወንጌል ረገድ ዓላማቸው ...*

በሐዋ. 16 ውስጥ ለፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ጅማሬ መንስዔ የሆኑ ነጥቦችን እናገኛለን። ሁሉንም በጥልቅ ባናይም ዋና ዋና ነጥቦችን እንዳስሳለን። እነዚህ ነጥቦች ልክ ወደላይ እንደሚወጣ እንደ ደረጃ ናቸው።

(1) በመጀመሪያ ጳውሎስ ወደ ፊልጵስዩስ የሄደው በእቅዱና በትልሙ አይደለም። አስቦበትና አስልቶ አይደለም። በሐዋ. 16፥6-12 እንደምናገኘው በእስያም በቢታንያም ቃሉን እንዳይናገሩ መንፈስ ቅዱስ ከልክሎአቸው ወደ ጢሮአዳ ሲደርሱ የመቄዶንያውን ሰው ራእይ አይቶ

ነው ወደ መቄዶንያ የሄደው። በቁጥር 6 እና 7 የምናገኘው መንፈስ ቅዱስ እንደከለከላቸውና እንዳልፈቀደላቸው ነው።

መንፈስ ቅዱስ ቃሉ እንዳይነገር፥ ወንጌል እንዳሰበክ ይከለክላል ማለት ነው? ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው የሚከለክልበት ጊዜና ሁኔታም ሊኖር እንደሚችል ነው። ወንጌል እንዳይሰበክ ፈልጎ ሳይሆን ጊዜና ቦታን የሚያውቅና የሚያመቻች እርሱ ነው። አንድን የወንጌል በር መዝጋቱ ሌላ የተከፈተ በር እንዳለ ለማሳየት ነው። የእስያና የቢታንያ በር የተዘጋው በመቄዶንያ ለወንጌል ይበልጥ የተዘጋጀ እርሻና ዘሩን ለመቀበል የተዘጋጀ አፈር መኖሩን መንፈስ ቅዱስ ስላወቀ ነው። ፈቃዱን ማወቅና በተከፈተ በር መግባት እንጂ ያገለገሉ እየመሰሉ መወዛወዝ ፍሬያማነት አይደለም። ጳውሎስ የሚመራውን መንፈስ ቅዱስን ለመስማትና ለመታዘዝ ጉጉና ዝግጁ የሆነ አገልጋይ በመሆኑ መንፈስ ቅዱስ አቅጣጫውን ብቻ ሳይሆን የተነሣበትንም ግብ ሲያስቀይረው ፈቃደኛ በመሆን ታዘዘ። መጀመሪያ አሳቡ የተተከሉትን አብያተ ክርስቲያናት በመጎብኘትና በማጠናከር መዞር ነበር። መንፈስ ቅዱስ ግን የራሱን እቅድና ወንጌል ያልተዘራበትንና ዘርን ለመቀበል ግን የተዘጋጀ ለም መሬት አሳየው። የወንጌል አገልጋይ አንድ በር ሲዘጋበት ማድረግ ያለበት በዚያው ጊዜ የተከፈተ በር አለና ያንን ለማየት ማማተር ነው እንጂ ያንን የተዘጋ በር በማንኳኳት ወይም ለመስበር በመታገል የተወደደ ጊዜና የከበረ ጉልበትና ንብረትም ማባከን የለበትም። አሳቡን አውቆ መሰማራትና በራስ ጉልበት ተፍ ተፍ ማለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ብዙ አገልጋዮች ሲጀምሩ ለምሪቱ ታዛዥ በመሆን ይጀምሩና አንድ ምቹ ቦታ ሲያገኙ ያ ሞቃት ስፍራ የዘላለም አልጋቸው ይመስል ተከናንበ መተኛት ያምራቸዋል።

> *የወንጌልን በር የሚከፍትና የሚዘጋ ጌታ ነው። አንድ በር ተዘጋ ማለት ሌላ የተከፈተ በር አለ ማለት ነውና ከተዘጋ በር ጋር ከመታገል በተከፈተው ለመግባት ማማተር ጥበብ ነው።*

ይህ የመንገድ መዘጋትና መከፈት በኢትዮጵያ የአንዲት ቤተ ክርስቲያን አጀማመርን ያስታውሳል። የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ የተጀመረችበት ታሪክ አስገራሚ ነው። የመጀመሪያዎቹ ሚስዮናውያን ሊሄዱ ተሰናድተው ጉዞ የጀመሩት ወደ ጂማ ነበረ። መንገድ ይመራ የነበረው አቶ ብሩ ዱባለ የተባለ ሰውም መንገዱን አዋቂ ነበረ። የሚሄዱበት መንገድ የብዙ ቀን ነበረና ሲሄዱ አልታወቃቸውም። ግን የብዙ ቀን መንገድ ሄደው ከምባታ አካባቢ ሲደርሱ ነበር የጂማ ሳይሆን የወላይታ መንገድ ላይ መሆናቸውን ያወቁት። ሰዎቹም የበሰሉ ነበሩና በእልከኝነት ወደኋላ ተመልሰን ወደ ጂማ እንሂድ ሳይሉ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ እንደወደደ እንዲመራቸው ጸለዩ። ከፊሉ ከምባታ ቀርተው ከፊሉ ወደፊት ገፍተው ወላይታ ላይ ሰፈሩና ወንጌልን አሮጡ። ከዚያ አገልግሎት እንደ ብርና ወርቅ እየተፈተኑ ያለፉ አገልጋዮች ነበር የወጡት፤ አጀማመሯ ግን እንደዚያ መንገድ የሳቱ በሚመስል ምሪት ነበር።

ጳውሎስና ሲላስ የመቄዶንያውን ራእይና የጥሪውን አሳብ እንደተረዱ ለአፍታም አልቆዩም። እንዲያውም ወዲያው በእግር ጉዞ ማድረጋቸውን ትተው ወደ ወደብ ወርደው መርከብ ያዙ። የጌታን አሳብ ከተረዱ ወደ ፈቃዱ ስፍራ መፍጠን እንጂ መንቀርፈፍ አያስፈልግም።

(2) በዚህች ከተማ ወንጌል ሲሰበክ ሰይጣን ዝም ብሎ አልተመለከተም። በዚህ ብቻ ሳይሆን በየትም ሰይጣን ነጻ የሚያወጣው የክርስቶስ ወንጌል ሲሰበክና ሰዎች ሲድኑ ዝም ብሎ አይመለከትም። በመጀመሪያ ወደሄዱበት የጸሎት ስፍራ ሲመላለሱ ስለ እነርሱ ትናገር የነበረች የምዋርተኝነት መንፈስ የነበረባት ገረድ ብዙ ቀን ስለነጳውሎስ እየጮኸች ትናገር ነበር። ትናገር የነበረውም፥ *የመዳንን መንገድ የሚነግሩአችሁ እነዚህ ሰዎች የልዑል አምላክ ባሪያዎች ናቸው* እያለች ነበር። የሚነግሩአችሁ የሚለውን አንዳንድ ትርጉሞች የሚነግሩን ነው የሚሉት፤ የሚነግሩን ካለች ራሷንም መጨመሯ ነው። በዚህ ትርጉም ራሷን የጨመረች አይደለችም። ደኅንነት አያስፈልጋትም ማለት ነው? ላዩን ሲታይ ይህች ገረድ የተናገረችው እውነት ይመስላል። መስተዋል ያለበት ግን የነገሩ እውነት መምሰል ሳይሆን የተናጋሪው ማን መሆን ነው። ሰይጣን ሰዎችን ከእውነት ለማራቅ እውነት የሚመስል ነገር መናገርና ማናገር ይችላል። ተአምራትም ማድረግ ይችላል። ለተራ ሰሚዎችና ተመልካቾች ይህች ሴትም እነጳውሎስም የየራሳቸውን አማልክት የሚናገሩና ከሁለት ተቀራራቢ አማልክት መርጠው የፈለጉትን ለመቀበል የማይገደዱ ያስመስለዋል። ደግሞም ስለ እነርሱ የተናገረችው እውነት ከመሰለ እርሷን እውነተኛ ነቢይት ያስመስላትና ተቀባይነቷ ይጨምራል።

> *ወንጌል በሚነገርበት ጊዜና ቦታ ሁሌም የሰይጣን ተግዳሮት አለ። ለስላሳና አሳሳችም ሊሆን ይችላል፤ ሻካራና ስደትና በትር ያለበትም ሊሆን ይችላል። ሰይጣን አመቺና ጠቃሚ የመሰለውን ከመጠቀም አይቦዝንም።*

እዚህ ላይ ነው ችግሩም መፍትሔውም። አንድ ነገር ሲነገር ነገሩን ብቻ ሳይሆን ምንጬንም ማየት አለብን። መናፍስትን መመርመር አለብን። ጳውሎስ በዚህ ጊዜ የገለጠው ሁለቱም አንድ ወይም ተቀራራቢ ያለመሆናቸውን ብቻ ሳይሆን እንዲያውም አንዱ የሌላው ተቃራኒ መሆናቸውን ነው። ይህን ያደረገው ደግሞ በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም ነው። ለጥቂት ቀናት ታገሡ፤ ይህን ያደረገው ለምን መሆኑን አናውቅም። እየጸለየበት ይሆን? ወንጌል ሳይሰበክ ከተማዋን ጥሎ የሚያስወጣ ስደት እንዳይደርስባቸው ይሆን? አናውቅም። ግን በመጨረሻ *ተቸገረና ዘወር ብሎ መንፈሱን፥ ከእርስዋ እንድትወጣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝሃለሁ አለው፤ በዚያም ሰዓት ወጣ።* ተቸገረ፥ ተረበሸ፥ ኮስኮሰው፥ አመመው እንደማለት ነው። ያኔ ገሰጸና አስወጣው። የሰይጣን ሥራ አይመቸን። ተመችቶን መቀመጥ ከያዝን የውሸት ምቾቱ ለጊዜው ነው። ኋላ ለዘለቄታው እየኮሰኮሰን ይኖራል። ለጊዜው እንዳይኮሰኩሰን ከበርኖሱ በታች ያለው ለስላሳ ከፈይ ዘለቄታ የለውም። ሰይጣን ካሞገሰን አይምሰለን። ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ እንደሚጥሏት ነው። ሊታረድ በመጫኛ የሚጣል በሬ ነው፤ ዶሮን እንደበሬ አተልቀው ካሞገሷት ትኮራለች ብቻ ሳይሆን ዘና ትላለች፤ ትጥቋን ትፈታለች። ሸንገላውን አንሳተው። ጳውሎስ አወቀው፤ ገሰጸው፤ አስወጣው።

ከዚህ ሳንወጣ ማየት ያለብን ሌላ ነገር ሰዎች ሰዎችን የሚመለከቱበት እይታ ነው። በተለይም የገረዷ ባለቤቶች። ገረዲቱ ለነዚህ ሰዎች የጥቅም ማግኛ መሣሪያ ብቻ ነች። ገንዘብ እስካስገኘች ትያዛለች ትጠበቃለች። ጨካኝ ባለቤቶች ናቸው። በመዳኗና ነፃ በመውጣቷ የሚከፋቸውና ነፃ እንድትወጣ የረዷትን ሰዎች ከመጉዳት የማይመለሱ ናቸው። የጌርጌሴኖኑ ሰው ነፃ ሲወጣ አጋንንቱ ወደ እሪያዎች ገብተው ነበር። ለኢየሱስ አንድ ሰው ከብዙ ሺህ እሪያዎች የከበረ ነው። እንዲያውም ለውድድርና ለንጽጽር አይቀርቡም። ሰዎችን እንደ እግዚአብሔር አምሳል መመልከት በረከት ነው።

(3) ከዚህ በኋላ 3ኛው ደረጃ ተወጣ። ጥሬ ስደት ተጀመረ። ሰይጣን ሲሆንለት ማታለል ሳይሆንለት ሲቀር ማሳደድ ይጀምራል። ከሁለት አንዱ ብዙ ጊዜ ይሠራለታል። ለሰነፎች ማታለልና መሸንገል ይሠራለታል። ለፈሪዎች ደግሞ ማሳደድ ይሠራለታል። የመጀመሪያዎቹ የስደት መሣሪያዎች የገረዲቱ ጌቶች ናቸው። አጋንንቱ ሲወጣ የትርፋቸው ተስፋ ወጣ። ቁጥር 19፥ *ጌቶችዋም የትርፋቸው ተስፋ እንደ ወጣ ባዩ ጊዜ ጳውሎስንና ሲላስን ይዘው ወደ ገበያ በሹማምት ፊት ጐተቱአቸው፤* ይላል። አንዳንድ ሰዎች ሰዎችን የጥቅም ማግኛ መሣሪያ ብቻ አድርገው ይመለከታሉ። ይህች ገረድ ለጌቶቿ (ከአንድ በላይ ናቸው፤ አዋጥተው የገዟት ሳትሆን አትቀርም) የገንዘብ መሥሪያ ብቻ ናት። ገንዘብ እስካስገኘች ድረስ የአጋንንት መጨፈሪያም ብትሆን ደስታቸው ነው። በመዳኗና ነጻ በመውጣቷ የሚከፋቸውና ነጻ ያወጧትን ከመጉዳት የማይመለሱ ናቸው። በሉቃ. 8፥26-39 በጌርጌሴኖን አጋንንት ያደሩበት ሰው ነጻ መውጣት ከዚህ ጋር ይቀራረባል። አጋንንቱ ወጥተው ወደ እሪያ ሲገቡና እሪያዎቹ ወደ ባህር ሲገቡ የአገሩ ሰዎች ወደ ኢየሱስ መጥተው

ከእነርሱ እንዲሄድ ለመኑት። ቀድሞ ለሰውየው ያዘነ፥ ከዳነ በኋላም በመዳኑ የተደሰተከመካከላቸው ያለ አይመስልም።

የነጳውሎስን ስደት ጀማሪዎቹ ጌቶችዋ ይሁኑ እንጂ ሕዝቡም ሹማምቱም ተባባሪዎች ሆኑ። ክሳቸው ደግሞ መንፈሳዊ ይዘት ቢኖረውም ግላዊ ሳይሆን ፖለቲካዊ ነው። አቀራረባቸው መሰሪ ነው። ከአገልጋያቸው አጋንንት መውጣቱን አልተናገሩም።ይልቁንም ያቺን ገረድ የገንዘብ መሥሪያ አድርገው ሲጠቀሙባት እንደኖሩ አልተናገሩም። የራሳቸውን ገመና እንዲታይ ሳያደርጉ ነው፥ *አይሁድ ሆነው ከተማችንን ያናውጣሉ፤ ለኛ ለሮሜ ሰዎች (ዜጋዎች) ለመቀበልና ለማድረግ የማይፈቀዱ ልማዶችን ይናገራሉ።* የፖለቲካ ክስ አደረጉት። እነርሱ በጎን ሾልከው ተከሳሾቹና መንግሥት የሚጋፈጡበትን መንገድ ነው የመነጠሩት። ከዜግነትና ከፖለቲካ ጋር አቆራኙት።

በሐዋ. 16፥12 ስለ ፊልጵስዩስ፥ *እርስዋም የመቄዶንያ ከተማ ሆና የወረዳ ዋና ከተማና ቅኝ አገር ናት ተብሎአል።* የሮም ቅኝ ከሆነች የሮም ከተማ ናት። ስለዚህም የከተማዋ ነዋሪዎች የከተማዋ ነዋሪ በመሆናቸው ሮማውያን ናቸው ወይም የሮሜ ዜጋዎች ናቸው። የሮሜ ዜጋዎች የዜግነት መብትና ጥቅማቸውን፥ ኃላፊነትና ግዴታቸውን የሚያውቁ ናቸው። ጳውሎስም ራሱ ሮማዊ ዜግነት ያለው ሰው ነውና ይህንን ያውቃል። በሐዋ. 16፥35-40 ገዢዎቹ እነጳውሎስን ከእስር እንዲፈቱና እንዲለቀቁ በላኩ ጊዜ ሮማዊ ዜጋ ያለ አግባብ እንዳይንገላታ ሕጉ እንደሚከላከልለት ያውቃሉና የሮሜ ዜጋዎች እንደሆኑና በሕዝብ ፊት ያለአግባብ ተደብድበው አሁን ደግሞ በስውር ተፈትተው እንዲሄዱ መደረጋቸው አግባብ አለመሆኑን አሳወቁ። ይህ መሆኑ ሲታወቅ የሚገርም ነገር ሆነ፤ *የሮሜ ሰዎችም እንደ ሆኑ በሰሙ ጊዜ ፈሩ፤ መጥተውም ማለዱአቸው፥ አውጥተውም ከከተማ ይወጡ ዘንድ ለመኑአቸው። ከወኅኒውም ወጥተው ወደ ልድያ ቤት ገቡ፥ ወንድሞችንም ባዩ ጊዜ አጽናኑአቸውና ሄዱ ይላል።* በሐዋ. 22፥24-30 ጳውሎስ ሮማዊ ዜግነቱን እንደገና ሲጠቅስ እናነብባለን። ጳውሎስ ዜግነቱን ሲያስፈልግ ቢጠቀምበትም ለወንጌሉ መነገርና ክርስቶስን ለመምሰል ሲል ግን አልተጠቀመበትም። ዜግነት ጠቃሚ ነገር ነው፤ ግን ሰማያዊ ዜግነት ከምድራዊ ዜግነት በላይ ነው። ሮማዊ ዜጋ ከሆነ ቀድሞ ሲደበደብ ለምን ዝም አለ?

በፊልጵስዩስ የጠቀሰበትን ሁኔታ ስናይ ከመንገላታት እንዲጠበቅ ሲል ቀደም ብሎ መናገር ሲችል አለመጥቀሱ ኋላ በፊል. 3፥20 *እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፥ ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን* ብሎ ለፊልጵስዩስ ሰዎች ከሚያስተምራቸው ትምህርት ጋር የተስማማ ነው። አገራችን የሚለው ቃል መኖሪያን ሳይሆን መኖርን ወይም አኗኗርን አካሄድን ዜግነትን የሚያሳይ ነው። ዜግነታችን እንደማለት ነው። ከዐውዱ (3፥1-19) ስንረዳም ምድራዊ ከሆኑ ሰዎች የመስቀሉ ጠላቶች ጋር ነው እያስተያየ ያለውና ስለ አገር አለመናገሩ ይስተዋላል። አንዳንድ ትርጉሞችም ይህንን አገራችን የሚለውን ቃል ዜግነት፥ አካሄድ፥ አነጋገር ብለው ነው የተረጎሙት። እርግጥም ቃሉ (πολίτευμα) ፖለቲካ ከሚለው ጋር የተቀራረበ ነው። የጳውሎስ ከሳሾችም ክሳቸውን ፖለቲካዊ ያደረጉት ይህንን አካሄድ በተመለከተ ነው፤ *ለኛ ለሮሜ ሰዎች (ዜጋዎች) ለመቀበልና ለማድረግ የማይፈቀዱ ልማዶችን ይናገራሉ።* ይህ ከአካላዊ አገር ይልቅ ከአነጋገርና ከአመላለስ ጋር የተቆራኘ ነው። የሚያስደንቀው ግን ጳውሎስ ሮማዊ ዜግነቱን ሲጠቅስ መጀመሪያውኑ ከመደብደብና ከመንገላታት ሊከላከል አልተጠቀመበትም።

(4) የሰዎች እውነተኛ ማንነት የሚወጣው በሚደርስባቸው ነገር ነው። ልክ የገረዷ ጌቶች ጥቅማቸው ሲነካ ነው የጦፉትና ሰዎችን አስተባብረው የተነሡባቸው። በሌላ በኩል ደግሞ የነጳውሎስ እውነተኛ ማንነትም በዚህ ጊዜ ወጣ። ሐዋ. 16፥23-25 *በብዙም ከደበደቡአቸው በኋላ ወደ ወኅኒ ጣሉአቸው፥ የወኅኒውንም ጠባቂ ተጠንቅቆ እንዲጠብቃቸው አዘዙት። እርሱም የዚህን ዓይነት ትእዛዝ ተቀብሎ ወደ ውስጠኛው ወኅኒ ጣላቸው፥ እግራቸውንም በግንድ አጣብቆ ጠረቃቸው። በመንፈቀ ሌሊት ግን ጳውሎስና ሲላስ እየጸለዩ እግዚአብሔርን በዜማ ያመሰግኑ ነበር፥ እስረኞቹም ያደምጡአቸው ነበር ይላል።* ውስጣዊ ማንነት እውነተኛ ማንነት ነው። እነጳውሎስ ተጎትተዋል፤ ተገፍፈው ተደብድበዋል፤ ወደ ወኅኒ ተጥለው በውስጠኛው ክፍል እግራቸው በግንድ ተጠርቆአል። ግን ምን ያደርጉ ነበር? ይጸልዩ፥ እግዚአብሔርንም በዜማ ያመሰግኑ ነበር።

በልቡ ሰላም የሌለው ሰው በሁከት ጊዜ ሊረጋጋ አይችልም። በልቡ ደስታ የሌለው ሰው በምሬት ሰዓት ማመስገን አይችልም። ያውም በዜማ። ደስ ያለው ማንም ቢኖር ይዘምር ነው ቃሉም የሚለው። ስለዚህ የደረሰባቸው ነገር ከባድና አስጨናቂ ቢሆንም እነ ጳውሎስ ያስደሰታቸው ነገር አለ ማለት ነው። በአምላካቸው ፈቃድ መካከል መሆናቸው ያስደስታቸዋል። ለወንጌል ሲሉ መከራን መቀበላቸው ያስደስታቸዋል። ማንነታቸው እየተፈተነ፥ እየነጠረ መሆኑን ማወቃቸው ያስደስታቸዋል። ስለዚህ ቢዘምሩ ይገባቸዋል።

*የሰዎች እውነተኛና ውስጣዊ ማንነት የሚወጣውና በጉልህ የሚታየው በሰላም ሳይሆን በመከራ ጊዜ፥ በደስታ ሳይሆን በኀዘን ጊዜ፥ በድሎት ሳይሆን በእጦት ጊዜ ነው። የአንዳንዶቹ ቀድሞም እዚያ የነበረ ነውና ጎልቶ ይታያል።*

(5) እግዚአብሔር ወንጌሉ እንዲሰማ ፈቃዱን ሲፈጽም ተአምራትንም ይጠቀማል። ሐዋ. 16፥ 26-30 26 በራእይ አመልክቶ አድርሶአቸው አልተዋቸውም። የመሬት መናወጥ ሆነና በዚያም ሌላ የወንጌል በር ተከፈተ። የወኅኒው ደጆች ብቻ ሳይሆኑ የወንጌል ደጆችም ተከፈቱ። የሰንሰለት እስራት ብቻ ሳይሆን የሰይጣን እስራቶችም ሊፈቱ ጀመሩ። መጀመሪያ ለአንድ ሰው ከዚያ ለቤተ ሰቡ መዳን ሆነ። በዚህ አላበቃም። እግዚአብሔር ለአንድ ቤተ ሰብም መዳን መሬትን ማናወጥ ይወዳል።

የእግዚአብሔር አሠራር ያስገርማል። አንዳንዴም አይገባም። ኋላ መሬት ሊያንቀጠቅጥና ሊያናውጥ፥ መዝጊያዎችን ሊከፍት፥ ሰንሰለቶች ሊሰብርና እስራት ሊፈታ፥ ግን አስቀድሞ ባሪያዎቹ፥ ልጆቹ እንዲገፉ፥ እንዲደበደቡ፥ መከራ እንዲቀበሉ፥ እንዲጠረቁ አደረገ። አንዳንዴ የሚያደርገው ነገር ባይገባንም እርሱ ግን የሚያደርገውን የሚያውቅ አምላክ ነው። የሚያደርገውን ማወቅ ብቻ ሳይሆን ለምን እንደሚያደርግም የሚያውቅ አምላክ ነው። የኛ ትንሽ አእምሮ መረዳት ባልቻለው ነገር ሁሉ አጉረምራሚዎችና አጉል ጥያቄ ጠያቂዎችና ከሳሾች አንሁን። ከታመምን ለምን? ካጣን ለምን? ከተሰደድን ለምን? ከተፈተንን ለምን? ለምን? ባዮች አንሁን። መጠየቁ ሳይከፋ ከእግዚአብሔር ጋር ጥለኞች አንሁን።

(6) ሌላው ለፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ጅማሬ መረማመጃው ለጥቂት ሴቶች የተነገረው ወንጌል ነው። ጳውሎስ በራእዩ እንዳየው ጌታ ወደዚያ የጠራው እንደሆነ በመረዳት አቀና። እውነትም በዚህ ከተማ ወንጌልም፥ ወንጌል የወለደው ስደትም ነበረ። በሐዋ. 16፥13-15 እንደምናገኘው እነጳውሎስ ለተሰበሰቡት ሴቶች ተናገሩ። ሴቶቹ ለምን እንደተሰበሰቡ አልተጻፈምና አናውቅም። ለሴቶቹ 'ሰበኩን' ሳይሆን 'ተናገርን' ማለቱ በሚገባቸው ቀላል ቋንቋና አቀራረብ ወንጌልን መናገሩ ነው። ሴቶች ናቸው ብሎ ወንዶችን ፍለጋ አልሄደም። ከውጤቱ እንደምንረዳው በዚያ ቀን አንዲት ሴትና ቤተሰቧ ዳኑና ተጠመቁ። የከተማዋ ቤተ ክርስቲያን አጀማመር ከእንዲህ ያለ ቀላል አነሣስ ነበር። ከአንዲት ሴትና አንድ ቤተ ሰብ መዳን ነው የተጀመረው። የተጀመረውም በቤቷ ነበር። ስለ ልድያ በሐዋ. 16፥14 ቃሉ ሲናገር፥ *ትሰማ ነበረች፤ ጳውሎስም የሚናገረውን ታዳምጥ ዘንድ ጌታ ልብዋን ከፈተላት።* ይላል። ጳውሎስ ሲናገር ጌታ ልቧን ከፈተላት። የተከፈተ ልብ የሚገኝበትን አናውቅምና ቃሉን ሳንታክት እንዝራ። በማቴ. 13 ጌታ የዘሪውን ምሳሌ ሲያስተምር ይህን

*የተከፈተ ልብ የሚገኝበትን አናውቅም። ልብን የሚከፍት እግዚአብሔር ነው። ማድረግ ያለብን ሳንታክት የቃሉን ዘር መዝራት ነው።*

ነበር ያሳየው። ሁሉ አፈር መልካም አይደለም፤ ግን መልካም አፈርም አለ። ከላይ አይተን የትኛው የቱ መሆኑን አናውቀውም። በማቴ. 13 እንደምናገኘው ዘር የሚያርፍባቸው አራት ዓይነት አፈሮች አሉ። አንዱ በእግር የተረጋገጠ መንገድ፥ ሌላው ውኃ የሚቋጥር ጭንጫ፥ ሌላው አብሮት የሚበቅል እሾህ ያለበት አፈር፥ ሌላው 30፥ 60፥ 100 አፈር ነው። ከላይ ሲታይ ሁሉ አፈር ነውና እኛ የአፈሩን መልክ ብቻ ከላይ እናያለን፤ እርሱ ግን የአፈሩን ልስላሴና ዘሩን ለመቀበል ጊዜው መሆንና አለመሆኑን ያያል። ለዚህም ነው አንድ በር ዘግቶ ሌላ ከፍቶ ወደዚህ የላካቸው።

የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ጅማሬ እንዲህ ነው። እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን የተጀመረችበትን ታሪክ ብንመረምር ሁሏም የሚያስደስት ታሪክ አላት። አንዳንዱ ከስደት ጋር የተቆራኘ ነው። አንዳንዱ ከመከራና ከእጦትጋር የተያያዘ ነው። የአንዳንዱ ከምሪትና ከመታዘዝና ዋጋ ከመክፈል ጋር የተያያዘ ነው። የሰዎች አሳብ እየቀረ የእግዚአብሔር እየቀደመ የተከናወነበት ነው። የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን በመለኮታዊ ምሪትም በስደትም ውስጥ ነበር የተጀመረችው።

እግዚአብሔር ከአርያም ይባርካችሁ። © ዕዝራ የስነ ጽሑፍ አገልግሎት / ዘመ






አንድ እንቁላል
. . . መሃል
ላመል አድርጎ
. . . ጣል
አምስት ዳቦ ከላይ
አምስቱን ከስር
አድርጎ ድርድር
እንዲህ ሆነ ኑሮ
መዝሙረ ዘንድሮ

የዘንድሮ መዝሙር ቃላቷ ሰባት
አስራ አንድ ጊዜ እንደጋግማት
ባስራ ሁለተኛው ወይ እሷ ወይ እኛ
ወድቀን እንቀራለን እንዳገሬ ጌኛ





እነዚህ ሁለት ምስሎች አንድ የሦራ ባልደረባዩ ከሞንታና አንሦቶ ያሳየን ናቸው።

ይህ ሙስ(moose)የተባለ የዱስ እንስሳ ሳያስብ ወደ ሰንጣቃው መሬት ገብቶ መውጣት አቅቶት እዚያው ሰንብቶ፥ እዚያው ሞቶአል። በወጉ እንኳ አልተቀበረም።

መንገዳችንን እያየን የምንሄድ ነን? የምናይበት መሣሪያስ አለን?

*ሕግህ ለእግሬ መብራት፥*

*ለመንገዴ ብርሃን ነው።*

መዝ. 119፥105